*Ethiop.j.lang.cult.commun. June 2026, 11*(1): 26-46
*ISSN: 2518-2919*

*Bahir Dar University-Faculty of Humanities*
DOI 10.20372/ejlcc.v11i1.3052

**Research Article** **Open Access**

# Gender role construction through birth ritual in Dorze community

**Atsede Yaregal Fentie[1] Guday Emirie Kassahun[2] Waltenigus Mekonnen Tegbaru[3]**

[1,3] Department of Folklore, Faculty of Humanities, Bahir Dar University, Bahir Dar, Ethiopia

[2]Department of Social Anthropology, College of Social Science, Addis Ababa University, Ethiopia

## Abstract

This study examines the construction of gender roles within the Dorze community through the lens of birth ceremonies. It aims to identify the gender roles reflected within these ceremonies and reveal the values associated with them. The study employs a qualitative research design, utilizing data gathered from both primary and secondary sources. Data were collected through interviews, focus group discussions, observations, and document reviews. The gathered information was then analyzed within the frameworks of Social Constructionism and Symbolic Interactionism theories. According to the analysis the choice of birthing location, expressions of joy, Seating arrangements for guests, the reception of the paternal grandfather and Postpartum events serve as key indicators of gender roles within the community's birth ceremonies. The findings confirm that masculinity is prominently associated with roles of ownership, inheritance, and decision-making, while femininity is framed primarily through the role of caregiving.

**ARTICLE HISTORY**
Received: September, 2025
Revised: December, 2025
Acceptted: January, 2026

**Keywords**: Gender, Gender Role, Birth Ritual, Breadwinner, Caregiver, Dorze

**Citation:** Atsede Yaregal Fentie, Guday Emirie Kassahun & Walteniguss Mekonnen Tegbaru. (2026). Gender role construction through birth ritual in Dorze community, *EJLCC.11* (1).26-46.
DOI 10.20372/ejlcc.v11i1.3052

CONTACT: Atsede Yaregal Fentie, Email: atsemill@yahoo.com; PhD Candidate, Department of Folklore , Faculty of Humanities, Bahir Dar University, Bahir Dar, Ethiopia



©2026 The Author(s). Published by Bahir Dar University, Faculty of Humanities.
This is an open access article distributed under the terms of the Creative Commons attribution license (http://creativecommons.org/licenses/by/4.0/), which permits unrestricted use, distribution, and reproduction in any medium, provided the original work is properly cited. The terms on which this article has beenpublished allow the posting of the accepted Manuscript in a repository by the author(s) or with their consent.

*Ethiop.j.lang.cult.commun. June 2026, 11*(1): 1-25
*ISSN: 2518-2919*
*Bahir Dar University-Faculty of Humanities*
DOI 10.20372/ejlcc.v11i1.3052

# የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች አቀራረፅ በዶርዜ ማህበረሰብ የወሊድ ከበራዎች ማሳያነት

*ይህ ጥናት የዶርዜ ማህበረሰብ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎችን አቀራረፅ በወሊድ ከበራው አማካኝነት የሚመረምር በከበራዎች ውስጥ የሚንጸባረቁ የስርዓተ-ፆታዊ ሚናዎችን የመለየት እና ከስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ጋር የተያያዙ እሴቶችን የመግለጥ ንዑሳን ዓላማዎች አሉት፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ሲሆን ከቀዳማይ እና ከካዕላይ የመረጃ ምንጮች በተገኙ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ መረጃዎቹ በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ በምልከታ እና በሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችም በማህበራዊ ግንባታ እና በትዕምርታዊ መስተጋብር ንድፈሃሳቦች ተቀንብበው ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ ትንተና መሰረት፤ የዶርዜ ማህበረሰብ በሚከውነው የወሊድ ከበራ ውስጥ የተስተዋሉ የመውለጃ ቦታ ምርጫ፣ የደስታ አገላለፅ፣ የእንግዳ አቀማመጥ አቅጣጫ፣ የወንድ አያት አቀባበል እና ድህረ ወሊድ ሁነቶች የማህበረሰቡን የስርዓተ-ፆታ ሚናን አመላካች ሆነው ቀርበዋል፡፡ ከጥናቱ ውጤት በመነሳትም፤ ወንድነት ከባለቤትነት፣ ከወራሽነት እና ከውሳኔ ሰጪነት ጋር ከተያያዙ ሚናቸው ላይ ጎልቶ ሲታይ ሴትነት ደግሞ ከተንከባካቢነት ሚና አንፃር መቃኘቱ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡*

## መግቢያ

ይህ ጥናት የስርዓተ-ፆታ ሚና በወሊድ ከበራዎች ውስጥ እንዴት እንደተቀረፀ የሚያሳይ ነው፡፡ የአንድ ማህበረሰብ የስርዓተ-ፆታ ስሪትም በተለያዩ የፎክሎር አይነቶች ውስጥ የሚገለጥ ሲሆን ከበራ አንዱ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም ከሽግግር ከበራዎች ውስጥ አንዱ በሆነው የወሊድ ከበራ ላይ ነው፡፡ የወሊድ ከበራ የህይወት ጅማሬ ሁነትን እንደመያዙ ለስርዓተ-ፆታ ሚና አሰጣጥም እንደ መነሻ የሚታይ ነው(Blakemore et al., 2009)፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የዶርዜ ማህበረሰብ በሚከውነው የወሊድ ከበራ ውስጥ ስርዓተ-ፆታዊ ሚናዎች እንዴት እንደሚቀረፁ ያሳያል፡፡ ጥናቱ የሚካሄድበት የዶርዜ ማህበረሰብ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ጋሞ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ በጨንቻ ወረዳ ውስጥ ይገኛል፡፡

## የጥናቱ ዳራ

ስርዓተ-ፆታ(Gender) የተለያዩ ዘርፎችን እና ምሁራንን የሚመለከት መልከብዙ እሳቤ እንደመሆኑ በጥናት ታሪኩ ውስጥ የተለያዩ አተያዮች እና የጥናት ትኩረቶች መነሳታቸው ይጠቀሳል፡፡ እንደ ርዕሰ ጉዳይ መታየት የጀመረው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ሲሆን (Kousaleos, 1999; Sawin 1997; Pilcher & Whelehan, 2004) በመጀመሪያዎቹ ዘመናት የነበሩ ጥናቶች ዋና ማጠንጠኛቸው የፆታ ልዩነት ምክንያቶችን በማጥናት ላይ ነበር፡፡ በመጀመሪያነት የሚጠቀሱትም በዋናነት በህክምና ባለሞያዎች ይተኮርበት የነበረው ስነሕይወታዊ አተያይ ነው፡፡ የዚህ እሳቤ ዋና ትኩረትም የፆታ ልዩነት ጉዳይ ተፈጥሯዊ በሆኑ የስነህይወት እና የሆርሞኖች ልዩነት የሚያመጡት ክስተት ነው የሚል ሃሳብን የሚያራምድ ነው (Bem, 1994; Risman, 2018)፡፡

ቀጥሎ የተነሳው ስነልቡናዊ አካሄድም ምንም እንኳን የመመዘኛ አይነቱ እና አተያዩ ይለይ እንጂ፤ የሴት እና የወንድ ልዩነት ምክንያት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከቀደመው ጋር ይዛመዳል፡፡ በስነልቡና አጥኚዎች የተቀነበበው ይህ አተያይ ደግሞ የፆታ ሚናን አመለካከት በስነልቡናዊ መለኪያዎች በማየት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በመሆኑም፣ ስርዓተ-ፆታን እንደ ግል ባህርይ (personality trait) የሚወስድ ነው፡፡ ለዚህ ንድፍ መነሳትም በዘመኑ ሴቶች ወደ ሳይንሱ ዘርፍ የመግባት እንቅስቃሴ እና ሁለተኛው የእንስታይ እንቅስቃሴ ያስነሳው ማዕበል አስተዋፅዖ ማድረጉ ይጠቀሳል (Risman & Davis, 2013)፡፡ ይህ አተያይ የግለሰቦችን ባህርያት በመለካት ሂደት ውስጥ በተለይ መለኪያዎቹ በራሳቸው በግለሰቡ ባህርይ ውስጥ የሌሉ ትርጓሜዎችን መፍጠር በመጀመራቸው ለትችት ተዳርጓል፡፡

ባህል ለስርዓተ-ፆታ ግንባታ ዋነኛው ጉዳይ መሆኑን ዋና ማጠንጠኛ አድርጎ የተነሳው ሌላኛው አተያይ ደግሞ ማህበራዊ ግንባታ ይባላል፡፡ በርግጥ ለዚህ መላምት እንደ ዋና መሰረት ባህል (Wienclaw, 2011) ተደርጎ ይነሳ

እንጂ ሀይማኖት (Juschka, 1999; Klingorova & Havlicek, 2015; Woodhead, 2012) እና ታሪክም በስርዓተ-ፆታ ግንባታ ውስጥ የራሳቸው ድርሻ አላቸው፡፡ እንደ Woodhead (2012) ሃሳብ ስርዓተ-ፆታ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ የተገናባ ውስብስብ መሆኑን በማንሳት ሀይማኖትም የዚህ አካል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የማህበራዊ ግንባታ አተያይ ትኩረት የሚያደርገው ሴቶች እና ወንዶች የሚኖራቸው ፆታዊ ማንነት የሚቀዳው ከሚያድጉበት ማህበረሰብ ባህል ነው በሚል ስርዓተ-ፆታን ማህበረሰብ ሰራሽ አድርጎ የሚቀበል እሳቤ ነው (Sawin, 1997)፡፡ የፆታ ሚና የመጠሪያ ለውጥ ተደርጎበት ወደ ስርዓተፆታ የተቀየረበት እና በዘመኑ የተነሱ የስልጣን(Power) እና የፆታ እኩልነት ጉዳይ ዋና ማጠንጠኛ ሆነው የመጡበት ንድፍም ጭምር ነው (Risman & Davis, 2013)፡፡ የማህበራዊ ግንባታ አተያይ መምጣት በተለይ ሴትነት እና ወንድነት እንደየማህበረሰቡ ርዕዮተ ዓለም የሚቀነበብ እና የሚገነባ ነው የሚል ሃሳብን የያዘ እንደመሆኑ፤ የፆታን እና የስርዓተ-ፆታን እሳቤ የቀነበበ ንድፍ ነው ማለት ይቻላል (Lawton & Primiano, 1996)፡፡ ይህን ም የስርዓተፆታን መልከ ብዙነት እና ማህበራዊ አውዳዊነት ጎልቶ እንዲወጣ እና እንዲታይ ማድረጉ ይገለፃል(Helgeson, 2012)፡: ስርዓተ-ፆታ ማህበረሰብ ሰራሽነቱን ሳይለቅ በማህበረሰቡ የዕለት ተለት መስተጋብር ውስጥ የሚተገበር እና ህልውናውንም በዚሁ ክዋኔ ውስጥ የሚያስጠብቅ ፅንሰሃሳብ መሆኑን ደግሞ West እና Zimmerman(1987) ይገልፃሉ፡:

በመቀጠልም የስርዓተ-ፆታ ጉዳይ ከማህበራዊነቱ በዘለለ የመዋቅር ጉዳይ ነው የሚል ሃሳብን የያዘው የመዋቅራውያን እይታ 1980ዎቹ ላይ ብሏል(Risman & Davis, 2013)፡፡ ስርዓተ ፆታን እንደ ማህበራዊ መዋቅር የሚያየው ይህ ንድፍ የስርዓተ-ፆታ ጉዳይ በዋናነት በግለሰባዊ፣ መስተጋብራዊ እና ተቋማዊ ደረጃ የሚታይ መሆን አለበት የሚል ሃሳብን የያዘ ነው፡፡ በዕለትተለት ማህበራዊ ህይወት እና ማህበራዊ መዋቅር ውስጥ ሰርፆ የሚገኝ ራሱን የቻለ ተቋም መሆኑን በማንሳት፣ ስርዓተ-ፆታ እንደ ተቋም መታየት እንዳለበት የሚያነሱት Lorber (1994)፤ ስርዓተ-ፆታ እንደ ተቋም ለግለሰቦች የሚጠበቁ ተግባራትን እና ሃላፊነቶችን የሚያበጅ፣ የማህበረሰቡን የእለት ተለት ህይወት የሚቆጣጠር እና በማህበረሰቡ ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ የተገነባ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ በRisman(2018) የተነሳው ስርዓተ-ፆታን እንደ ማህበራዊ መዋቅር የማየት እሳቤ፤ ስርዓተ-ፆታ በማህበረሰቡ ውስጥ እንደሚገኙ መዋቅሮች ሁሉ እንደ አንድ መዋቅር ራሱን ችሎ መታየት እንዳለበት ያነሳሉ፡፡ ይህም በግለሰብ፣ በማህበራዊ መስተጋብሮች እና በአጠቃላይ መዋቅራዊ ደረጃዎች ውስጥ ሰርፆ የሚገኘውን ስርዓተ-ፆታዊ ጉዳዮች ለማየት ያግዛል የሚል ሃሳብን ያነሳሉ (Risman, 2018) ፡፡

የ20ኛው ክፍለዘመን መጨረሻዎቹ አስርት ዓመታት የስርዓተ-ፆታ ጉዳይ በተለይ በጥቁር አሜሪካውያን እና ከ1980ዎቹ አጋማሽ በኋላ በመጡ

አፍሪካውያን አጥኚዎች ሌላ መልክ መያዝ የጀመረበት ዘመን ነው፡፡ ስርዓተፆታ በአለም ላይ በተመሳሳይ መልኩ ከመታየት ይልቅ ከሌሎች ማህበረሰብ ሰራሽ ልዩነቶች ማለትም እንደ ዘር፣ የቆዳ ቀለም፣ ጎሳ፣ ሃይማኖት እና መሰል ልዩነቶች ጋር ተሰባጥሮ መታየት እንዳለበት የሚሞግት አተያይ ነው፡፡ ይህም በተለይ በዘመኑ የነበሩ ቀደምት ጥናቶች የምዕራባውያን ርዕዮተ ዓለም የተጫናቸው እና የሌሎች ማህበረሰቦች መሰል ልዩነቶች የዘነጋ በመሆኑ፤ የስርዓተ-ፆታ ጥናት የአተያይ ለውጥ እንዲመጣ ምክንያት ሆኗል፡፡ ምንም እንኳን የአፍሪካ የስርዓተ-ፆታ ጥናት ታሪክ ከጥቁር አሜሪካውያን ጉዳይ ጋር ተያይዞ ቢነሳም፤ የራሱ የተለየ መልክ ያለው መሆኑ ይጠቀሳል (Lewis, 2005)፡፡ ከ1970ዎቹ በፊት የነበሩ ጥናቶች የቅኝ ግዛት ዘመን እንደመሆኑ የአውሮፓውያን የበላይነት ስሜት የተጫናቸው ሲሆኑ፣ በአውሮፓውያን የቅኝ ግዛት አስተዳዳሪዎችና አንትሮፖሎጂ ተመራማሪዎች የቀረቡ ናቸው (Lewis, 2005; Reddock, 2000)፡፡ ከግኝ ግዛት መክሰም በኋላ የመጣው የነፃነት ዘመንን ተከትሎ የመጡ ጥናቶችም የቀደመው ዘመን ላይ የተስተዋለውን የቅኝ ግዛት መንፈስ በማፍረስ እና ሃገርኛ የሆኑ ጉዳዮችን ማንሳት ላይ ወደ ማተኮር ዞረዋል፡፡ በመሆኑም የአፍሪካ የስርዓተ-ፆታ ጥናቶች በሌሎች ጥቁር አሜሪካውያን ካነሷቸው ሃሳቦች በተጨማሪ በአፍሪካ የነበረው ቅኝ ግዛት ያስከተላቸው ተብለው የሚታሰቡ ዘርፈ ብዙ ችግሮችንም ያቀፈ እንደነበረ ይጠቀሳል(Lewis, 2005)፡፡ በአጠቃላይ የስርዓተ-ፆታ ጥናት መነሻ ከሆነው ተፈጥሯዊ ገፅታ በመነሳት ቀስበቀስ እንደባህል፣ ታሪክ፣ ኢኮኖሚ እና መሰል ማህበረሰብ ሰራሽ ጉዳዮችን ወደ መተንተን የተሻገረበት ታሪካዊ ሂደት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም ስርዓተ-ፆታን ልንመረምርበት የምንችልባቸው የተለያዩ አተያዮች ሲኖሩ ዋናዎቹም የስልጣን መስተጋብር፣ ማህበራዊ ግንባታ እና ስብጥራዊ አተያዮች ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ጥናት የሚያተኩረው የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች እንዴት እንደተገነቡ በማሳየት ላይ እንደመሆኑ እና ይህንም ማህበረሰቡ በሚከውናቸው የወሊድ ከበራዎች የሚያይ በመሆኑ፤ ጥናቱ በማህበራዊ ግንባታ አተያይ ይቃኛል፡፡

ፎክሎር የአንድን ቡድን ርዕዮተ ዓለም የሚያሳይ መሆኑን Dundes (2007) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፈቃደ (2004) ኢጣልያዊውን የፎክሎር ምሁር ግራሚሽን በመጥቀስ ፎክሎር "... ቡድኖች ዓለምን የቀረፁበት፣ የተመለከቱበትና ዛሬም የሚያዩበት መንገድ (ርዕዮተዓለማቸው)...(115)" ሆኖ የሚይታይ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም የፎክሎር ዘርፎችን መመርመር አንድ ማህበረሰብ ስለ ስርዓተ- ዓለሙ ያለውን አረዳድ እና አገነባብ ለማግኘት እንደሚረዳ ያሳያል፡፡ እንደ ማህበራዊ ግንባታ አተያይ፣ ስርዓተ-ፆታ አንዱ ማህበረሰብ ሰራሽ ጉዳይ እንደመሆኑ፤ ማህበረሰቡን ስለ ስርዓተ-ፆታ ያለውን አተያይ እና አገነባብ ለማየት ፎክሎሩን መመርመር አይነተኛ መንገድ ሆኖ ታይቷል፡፡

የሰው ልጅ ሥርዓተ ዓለሙን ከሚገነዘብባቸው፣ ከሚቀርጽባቸውና ከሚገነባባቸው የፎክሎር ዘውጎች መካከል ከበራዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም የሰው ልጅ ሕይወትን እንዲገነዘብ የሚያደርጉ ቋሚ ሰነዶች መሆናቸውን Frobish (2004) ያስረዳሉ፡፡ እንደ Davis-Floyd እና Laughlin(2022) ሃሳብ ደግሞ ከበራዎች የአንድን ባህል መሠረታዊ እምነቶች እና እሴቶች ከማውጣት እና ከማሳዬት በተጨማሪ፤ እነዚህን እምነቶች እና እሴቶች ለማስተላለፍ፣ ለማጠንከር እንዲሁም ለመጠበቅ የሚያስችሉ ዘዴዎች ሆነው እንደሚያገለግሉ ይገልፃሉ፡፡ ይህም በተለይ የማህበረሰቡ አባላት ከባህሉ ጋር እንዲተዋወቁ፣ እንዲላመዱ እና እንዲዋሃዱ በማድረግ ረገድ ከበራዎች ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው አመላካች ነው፡፡

ከበራዎች ከሌሎች የፎክሎር ዘርፎች በተሻለ ስርዓተፆታን በመገንባት፣ በማስታወስ እና በማፅናት ረገድ ከፍተኛ ሚናን እንደሚጫወቱ Pollock (2004) ይገልፃሉ፡፡ በውስጣቸውም ቃላዊ፣ ድርጊታዊ እና ቁሳዊ ገፅታዎች ተሰናስለው የሚገኙባቸው እና ማህበረ-ባህላዊ ዳራው በሰፊው የሚስተዋልባቸው እንደመሆኑ ማህበራዊ እሳቤን ለመረዳት እና ለማግኘት ሁነኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡ በተለይም ከግለሰቦች የህይወት ለውጦችን ተከትለው በሚመጡ ከበራዎች ውስጥ ስርዓተ ፆታዊ ጉዳዮች በሰፊው ይስተዋላሉ፡፡ በአብዛኛው ማህበረሰብ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ አይቀሬ የሚባሉት የህይወት ክስተቶች ውልደት፣ ጋብቻ እና ሞትን የሚመለከቱ ናቸው (Bell, 1997)፡፡ እነዚህ ማህበራዊ ክስተቶችን ተከትሎ የሚመጡ ከበራዎች ደግሞ ስርዓተፆታዊ ሚናዎችን ለይተው በሚያሳዩ ሁነቶች የታጀቡ እና አይቀሬ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ከበራዎች ውስጥም የወሊድ ከበራ አንዱ ነው፡፡ ወሊድ ስነ-ህይወታዊ ክስተት ብቻ ሳይሆን ማህበረሰባዊ እና ባህላዊ ውቅርም እንደመሆኑ የማህበረሰቡን ማህበራዊ ማንነት እና ባህላዊ እሴቶችን በሚወክሉ ተያያዥ ምልክቶች እና ስነ-ስርዓቶች የተገነባ ነው(Van Beek, 2002)፡፡ በእንደዚህ አይነት ተፈጥሮን ከባህል በሚያስተሳስር ክስተት ደግሞ ጎልተው ከሚታዩ ጉዳዮች ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ሚና ጉዳይ አንዱ ነው፡፡

የስርዓተ-ፆታ ሚና አሰጣጥ እና ስሪት በተለይ የተለያዩ የሙያ መስኮች በስብጥር በሚገኙባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ጥብቅ እና ውስብስብ መሆኑ ይነገራል፡፡ እንደዚህ አይነት የሙያ ስብጥሮች ከሚገኙባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ የዶርዜ ማህበረሰብ አንዱ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በዋናነት በሽመና ስራ በኢትዮጵያ ደረጃ ስማቸው ከገነኑ የሙያ ባለቤቶች ውስጥ በቀዳሚነት የሚነሳ ማህበረሰብ ነው (Mathiszig, 2014)፡፡ ከዚህ የሙያ መስክ በተጨማሪም ማህበረሰቡ በእርሻም የሚተዳደር ሲሆን የሸክላ፣ የቆዳ እና የብረት ስራዎችም በተወሰነ መልኩ የሚገኙበት መሆኑ የሙያ ስብጥሩን ከፍ ያደርጉታል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ከእርሻ ስራ በተጨማሪ የሽመና ስራንም እንደ መተዳደሪያ የሚጠቀም መሆኑ የስርዓተ ፆታ ሚናውን ቅጥ(pattern) ለማየት አመቺ

ያደርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማህበረሰቡ ፆታዊ የስራ ክፍፍሉ(sexual division of labour) ጥብቅ እና ውስብስብ(strict and complex) መሆኑ (Olmstead, 1975; Getaneh, 2004; Hebo & Mahari, 2022) ማህበረሰቡን ለማጥናት ምክንያት ሆኗል፡፡

የዶርዜ ማህበረሰብን የሚመለከቱ በርካታ ጥናቶች አሉ፡፡ የእነዚህ ጥናቶች ትኩረትም ምጣኔ ሃብታዊ ገጽታ (Halperine & Olmstead, 1976)፣ የሴቶች ሚና እና ምጣኔ ሃብታዊ ገጽታ (Olmstead, 1975; Getaneh, 2004)፣ የሽመና ልማዱ (Mathiszig, 2014)፣ ባህላዊ መድሃኒት (Wagaye, 2016)፣ የቤት አሰራር (Olmstead, 1972)፣ ባህላዊ አስተዳደር ስርዓት (Freeman, 2002) እና የሴቶች ፆታዊ መብቶች ከባህሉ እና ህጋዊ አሰራሩ አንፃር (Getaneh, 2014) ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች የዶርዜን ማህበረሰብ በርካታ ገጽታዎች ያዩ ቢሆንም ከስርዓተ-ፆታ ጋር በተገናኘ ከተሰሩት ጥናቶች (Olmstead, 1975; Getaneh, 2004; Getaneh, 2014) በስተቀር ማህበረሰቡ ላይ ከመስራታቸው በስተቀር የዚህን ጥናት ርዕሰጉዳይ አልዳሰሱም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ሶስት ጥናቶች ደግሞ አንደኛ ትኩረታቸው ሴቶች ላይ ብቻ ማድረጋቸው፣ እንዲሁም የOlmstead(1975) እና የGetaneh(2004) ጥናቶች የሴቶችን ሚናን ከኢኮኖሚ አንፃር የተመለከቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን የስርዓተ-ፆታ አገነባብ በምልዓት ያሳያል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ስርዓተ-ፆታን የሚመለከቱ ስራዎች ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ የስርዓተ-ፆታ ልማድ ልዩነቶችን መነሻ ከሥር መሠረታቸው ማየት እንደሚገባ Giulian (2020)ይጠቅሳል፡፡ የአንድን ማህበረሰብ የስርዓተ-ፆታ ሚና ስሪት ለመረዳት ደግሞ ከበራዎችን መመርመር አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በወሊድ ከበራው ውስጥ የታዩ ስርዓተ ፆታን አመላካች ሁነቶችን እና ትዕምርቶችን በመተንተን የተጠኚውን ማህበረሰብ የስርዓተፆታ ሚናዎች ያሳያል፡፡

## የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በኢትዮጵያ የፎክሎር ጥናት ውስጥ ምንም እንኳን ስርዓተ-ፆታን የሚመለከቱ በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም የወሊድ ከበራን ከስርዓተ-ፆታ ሚና አንፃር የቃኘ ጥናት ግን አልተገኘም፡፡ ስርዓተ-ፆታዊ ሚናዎች በተፈጠሩበት ማህበረሰብ ባህል ውስጥ ስር ሰደው የሚገኙ እንደመሆናቸው፣ በተለያዩ ስርዓቶች፣ እምነቶች፣ ተቋማት እና ክዋኔዎች ውስጥ በሰፊው ይስተዋላሉ፡፡ ከበራዎች ደግሞ ከሌሎች የፎክሎር ዘርፎች በተሻለ ስርዓተፆታን በመገንባት፣ በማስታወስ እና በማፅናት ረገድ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታሉ (Pollock, 2004; Das, 2022; Naik & Sethi, 2025)፡፡ ከዚህ በመነሳትም የአንድን ማህበረሰብ የስርዓተ-ፆታ ሚና አገነባብ ለማየት ከበራዎችን ማጥናት የተሻለ እይታን ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

በሃገራችን የወሊድ ከበራን ትኩረት አድርገው የተጠኑ የተለያዩ ጥናቶች አሉ። እነዚህ ጥናቶችንም በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡- ጤና ተኮር እና ባህል ተኮር። በመጀመሪያው ክፍል የሚገኙ ጥናቶች በጤና ዘርፍ ባሉ ባለሞያዎች የተሰሩ እና ጥናቱ ባተኮረባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ የሚከወኑት የወሊድ ስርዓቶች ከጤና አንፃር ያላቸውን አንድምታ የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህ ጥናቶችም በ Solomon እና Tesfaye የተሰራው "Traditional practices during pregnancy and childbirth among mothers in Shey Bench District, South West Ethiopia(2022)"፤ በAynalem እና ሌሎች የተጠናው "Cultural Beliefs and Traditional Practices During Pregnancy, Child Birth, and the Postpartum Period in East Gojjam Zone, North west Ethiopia: AQualitative Study" (2023) ፣ እና በ Kitila እና ሌሎች የተጠናው "Folk Practice During Childbirth and Reasons for the Practice in Ethiopia: A Systematic Review"(2018) ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ጥናቶች ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ልማዳዊ ድርጊቶች በእናትዬው እና በህፃኑ ላይ ያላቸውን የጤና ተፅዕኖ በማሳዬት ላይ ያተኩራሉ።

ሌላው የወሊድ ስርዓትን ከሚዳስሱ ጥናቶች ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ባህላዊ ገፅታው ላይ ያተኮሩ የባህል ጥናቶች ናቸው። እነዚህ ጥናቶችም የAdane እና Melese "Birth ritual ceremony in Hadiya culture"(2023)፤ የእታገኝ አስረስ(2017) "የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፤ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ"፤ የድርብወርቅ ብፁ(2007) "የጉሙዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓት በማንዱራ ወረዳ" እና የአፀደ ተፈራ(2007) የዋግ ኽምራ የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ስነ-ስርዓት ፋይዳ ትንተና ጥናቶች ናቸው። እነዚህ ጥናቶች ባተኮሩባቸው ማህበረሰቦች ዘንድ ስላለው የወሊድ ከበራ ክዋኔ ከማብራራት በዘለለ፤ በክዋኔዎች ውስጥ ሰርፆ ስለሚገኘው የስርዓተ-ፆታ ሚና ያነሱት አንዳች ጉዳይ የለም። በመሆኑም ይህ ጥናት ይህንን ክፍተት በመሙላት በርዕሰ ጉዳዩ የጥናት ዘርፍ አንዳች አስተዋፅኦ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።

**የጥናቱ ዓላማ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዶርዜ ማህበረሰብ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች አቀራረፅ በወሊድ ከበራው አማካኝነት መመርመር ሲሆን በከበራዎች ውስጥ የሚንጸባረቁ የስርዓተ-ፆታዊ ሚናዎችን የመለየት እና ከስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ጋር የተያያዙ እሴቶችን የመግለጥ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችም ከቀዳማይ እና ካልዓይ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ ከቀዳማይ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት እና ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ በቃለመጠይቅ ዘዴም አስር ሴቶች እና አምስት ወንዶች በአጠቃላይ አስራ አምስት ሰዎች የተሳተፉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ስድስቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ እነዚህ የመረጃ አቀባዮችም ታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ ሲሆን ርዕሰ ጉዳዩን አስመልክቶ የማህበረሰቡን ባህል ጠንቅቀው እንደሚያውቁ የተመሰከረላቸው የማህበረሰቡ አባላት ናቸው፡፡ ይህ ዘዴም በተለይ ከበራውን አስመልክቶ ያሉ እሳቤዎችን፣ ፍቺዎችን እና አመለካከቶችን ለመረዳት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ሌላው አገልግሎት ላይ የዋለው የምልከታ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴም አራስ የሆኑ ሁለት ሰዎች ቤት በመገኘት የአራስ ቤት ድባቡን እንዲሁም በተጠኚው ማህበረሰብ የገበያ ቦታ በመገኘት ወላዶች ወደገበያ የመውጣት ስርዓትን ሲፈፅሙ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመኖሪያ ቤቶች፣ በገበያ፣ በለቅሶ ስርዓቶች፣ በመስቀል በዓላት ላይ በመገኘት የማህበረሰቡን የለት ተለት ህይወት ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

በቃለመጠይቅ እና በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ለማጥራት ይረዳ ዘንድ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡ ውይይቱም በሶስት ቡድኖች አማካኝነት የተከናወነ ሲሆን ሁለቱ በተለያዩ የእድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶች እንዲሁም አንዱ በወንዶች የተዋቀሩ ቡድኖች ናቸው፡፡ ይህም በዋናነት ብዥታ የነበረባቸውን አንዳንድ ሁነቶችን ግልፅ ለማድረግ ረድቷል፡፡

ሰነድ ፍተሻ ደግሞ ከካልዓይ ምንጮች የሚገኙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ሲውል በማህበረሰቡ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች እና ፅንሰሃሳባዊ ጉዳዮችን ለመቃኘት የሚያግዙ ፅሁፎችን በመቃኘት ጥናቱን ለማዳበር ያገዙ ሃሳቦች ተሰብስበውበታል፡፡

## ንድፈሃሳባዊ ማህቀፍ

የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች በተለያዩ ንድፈሃሳቦች ሊጠኑ ይችላሉ፡፡ ከነዚህ ንድፈ ሃሳቦች መካከል ደግሞ የማህበራዊ ግንባታ ንድፈሃሳብ አንዱ ነው፡፡ እንደ ስርዓተ-ፆታ ሁሉ የማህበራዊ ግንባታ ንድፈሃሳብ በይነዲሲፕሊናዊ እና መልከብዙ ነው፡፡ ይህ መልከብዙነቱም በዋናነት ነገሮች ከማህበረሰብ ማህበረሰብ፣ ከዘመን ዘመን እንዲሁም ከአውድ አውድ ያላቸው ትርጉም ወጥ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ በመሆኑም፣ አንድን ጉዳይ እነዚህን የተለያዩ ገፅታዎች ታሳቢ ተደርገው መጠናቱ ማህበረሰቡን፣ ዘመኑን እና አውዱን ያማከለ እውነታን እንድናገኝ ያስችለናል ተብሎ ይታመናል(Blakemore et al, 2009)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ መስተጋብርን፣ አውድን እና ሂደትን የሚይዘው ይህ ንድፍ፣ የስርዓተ-ፆታ ገዳዮችን ማህበረሰብ ሰራሽነት ላይ ማተኮሩ ለንድፉ

እንደጠንካራ ጎን ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑ እና እንዴት እንደሚገነባም ለመመርመር አመቺ በመሆኑ ለዚህ ጥናት ተመርጧል፡፡

ለዚህ ጥናት ማኼጃነት ሌላው የተመረጠው ንድፈሃሳብ ትዕምርታዊ መስተጋብር ነው፡፡ ይህ ንድፈሃሳብ ሰዎች እርስበርስ በሚያደርጉት ግንኙነቶች ውስጥ ትርጓሜን እንዴት እንደሚፈጥሩ የሚያሳይ ሲሆን ሰዎች ለተለያዩ ድርጊቶች የሚኖራቸው ትርጓሜ በትዕምርቶች አማካኝነት የሚገለጥ መሆኑን በሚመለከት እሳቤ ላይ ያተኩራል (Carter & Fuller, 2015)፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በተተኳሪው ማህበረሰብ ማህበራዊ መስተጋብር ጎልቶ በሚታይባቸው ከበራዎች እንደማተኮሩ እና ከበራዎች ደግሞ በትዕምርት በበለፀጉ ጉዳዮች የታሹ እንደመሆናቸው(Bell, 1997; Salamone, 2004; Sims & Stephens, 2005)፤ የማህበረሰቡን እሳቤ ለመረዳት ይህ ንድፈሃሳብ ተመርጧል፡፡

## የመረጃ ትንተና

ይህ ክፍል ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደቅደምተከተላቸው በማደራጀት ተተንትነው የሚቀርቡበት ነው፡፡ የወሊድ ከበራ በአብዛኛው ጊዜ ከእርግዝና ጀምሮ እስከ ድህረ ወሊድ ድረስ እንደየማህበረሰቡ ባህል መሰረት ረጅም ሂደቶችን የሚያለፍ ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም በዋናነት ከውልደት ጀምሮ ባሉ እና የስርዓተ-ፆታ ሚናን አመላካች የሆኑ ቃላዊ፣ ድርጊታዊ እና ቁሳዊ ሁነቶች ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ይተነተናሉ፡፡

### የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች በወሊድ ከበራዎች እንደታዩት

በዶርዜ ማህበረሰብ ዘንድ፤ መውለድ በክብር እና በደስታ ተቀባይነት ያለው ሁነት ነው፡፡ በተለይ ወንድ ልጅ መውለድ ዘር የመተካቱን እና ጎሳ የማስፋቱን ሚና ህልውና የሚያረጋግጥ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በርግጥ እንደዚህ አይነት እሳቤዎች በሌሎች ማህበረሰቦችም ዘንድ ተመሳሳይ ሆኖ እንደሚታይ ሌሎች ጥናቶች ያሳያሉ (Saikeneva, 2024; Maponya, 2021; Polit, 2016)፡፡ በዶርዜ ማህበረሰብ የወሊድ ከበራ ልማድ ውስጥ ወንድነት እና ሴትነት እንዴት እንደሚታይ የተገለጡባቸው በርካታ ሁነቶች ሲኖሩ እንደቅደምተከተላቸው በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

### ቅድመ - ወሊድ

በዶርዜ ማህበረሰብ ልማድ መሰረት አንዲት እርጉዝ ሴት መውለጃዋ ሲደርስ የተለያዩ ዝግጅቶች ይደረጋሉ፡፡ እነዚህ ዝግጅቶች በዋናነት የምግብ እና የቦታ ዝግጅቶች ናቸው፡፡ ለአራስ የሚሆኑ መጠጦች እና ምግቦችን በባል እናት በኩል የሚዘጋጅ ሲሆን ለዝግጅቱ የሚሆኑ ወጪዎች ደግሞ በባል ይሸፈናሉ፡፡ የመታረሻ ቦታ ዝግጅት በወንድ ቤተሰቦች ቤት ውስጥ የሚከናወን ሲሆን ወላዷ የምትታረስበት ቦታ ተለይቶ የመከለል፣ የእሳት ማንደጃ ቦታ የማዘጋጀት እንዲሁም ለእሳት የሚያስፈልጉ እንጨቶችን የማሰባሰብ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

በማህበረሰቡ የወንድነት እና ሴትነት ስሪትን ከሚያሳዩ ሁነቶች ውስጥ የመጀመሪያው ከመውለጃ እና ከመታረሻ ቦታ ምርጫ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በባህሉ መሰረት አንዲት ሴት መውለድ ያለባት በባሏ ቤተሰቦች ቤት ነው፡፡ ለዚህ እሳቤ የሚነሳው ምክንያትም ወ/ሮ መነን "የወንድ ቤት ደም በሴት ቤት አይፈስም ነውር ነው፡፡ ጎሜ[ጎሜ ደንብ በመተላለፍ የሚመጣ ሃጥያት ሲሆን ይህ ሃጥያትም አንዳች መቅሰፍት ወይም ችግር ፈፃሚው አለፍ ሲልም በቤተሰብ እና ማህበረሰብ ላይ የሚያስከትል ነው] ይሆናል በእሱ ቤተሰቦች ቤት ነው መወለድ ያለባት"(ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ አማራ፣ ጥቅምት፣ 2017 ዓ.ም.) በማለት ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ልጅን በሴት ቤተሰቦች ዘንድ መውለድ መቅሰፍትን በወላዷ ወንድ ቤተሰቦች ዘንድ እንደመጥራት ይቆጠራል (ወ/ሮ ፅጌ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ አማራ፣ መስከረም፣ 2018 ዓ.ም.)፡፡ ከዚህ በትይዩ አራሷ ልጇን ከማጥባት ውጭ የጡቷ ወተት ምንም ነገር ላይ እንዲፈስ አይፈቀድም፤ ያረክሳል፡፡ ይህም በተመሳሳይ ጎሜ ነው ተብሎ እንደሚታሰብ በቃለመጠይቁ ተነስቷል፡፡ Wood እና Eagly(2012) የትኛውም ባህል ደንቡ፣ ስርዓቱ እና ተቋማቱ ተጠብቀው እንዲቆዩ የሚያደርግበት የመቆጣጠሪያ ስርዓት እንዳለው በመጥቀስ በተለይ በስርዓተፆታ ሚና ዙሪያ የሚኖሩ እነዚህ የመቆጣጠሪያ ስርዓቶች ኢመደበኛ ቢሆኑም አንዳች ሃይል አላቸው ተብሎ የሚታመን መሆኑን ያነሳሉ፡፡ በተመሳሳይም በወሊድ ከበራው እንደታየው ነውር እንደ መቆጣጠሪያ ስርዓት ሆኖ ቀርቧል፡፡ በመሆኑም ልጅ የሚወለደው በአባት ቤተሰብ ዘንድ ነው፡፡ ይህም እናት ማህፀን ውስጥ ያለው ልጅ የአባት ዘር በመሆኑ፤ መወለድ ያለበት የአባቱ ዘር ባለበት ቦታ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ዘር የወንዶች መሆኑን፤ ሴቶች ደግሞ ዘርን ተቀብለው እና ለፍሬ አብቅተው ሰጪ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ይህም ወንድነትን ከዘር ባለቤት እና ዘር አስቀጣይነት፤ ሴትነትን ደግሞ ዘርን ተቀብሎ ለፍሬ ከማብቃት እና ከእንክብካቤ ጋር የሚያይዝ ሆኖ ታይቷል፡፡

**ጊዜ ወሊድ**

ይህ ክፍል ከወሊድ ዕለት ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ሁነቶችን የሚመለከት ሲሆን እነዚህ ሁነቶች በዚያን ዕለት የሚከወኑ ብቻ ሳይሆን ቀጣይ ቀናትም ሊከወኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ የወሊድ ቀን ዝግጅት ተደርጎበት የሚጠበቅ ቀን እንደመሆኑ በጉጉት የሚጠበቅ ሁነት ነው፡፡ በባህሉ መሰረት በዚህ ዕለት በሚኖሩ የማዋለድ ተግባራት ላይ የሚሳተፉ ሴቶች ናቸው፡፡ በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው በአሁኑ ሰዓት የጤና ተቋማት መኖርና በጤና ተቋም የመውለድ ግንዛቤ በመፈጠሩ ምክንያት ነፍሰጡሮች በጤና ተቋማት መውለድ የተጀመረ ሲሆን በፊት በነበረው ልማድ በወሊዱ ቀንም አዋላጅ፣ እትብት ቆራጭ እና እንግዴ ልጅ ቀባሪ የሆኑ ሴቶች በቤቱ ይገኛሉ፡፡ አዋላጇ ልጁ/ጅቱ በሰላም የመገላገል፤ እትብት ቆራጪ እትብቱን በትክክል የመቁረጥ እና የማስተካከል፤ እንግዴ ልጅ የምትቀብረው ሴት ደግሞ

የእንግዴ ልጁን ተቀብላ የመቅበር ሃላፊነት አለባቸው፡፡ አዋላጇ እና እትብት የምትቆርጠው በማህበረሰቡ በሙያቸው የሚታወቁ ሰዎች ሲሆኑ እንግዴ ልጅ የምትቀብረው ሴት ግን በአካባቢው ካሉ መውለድ ካቆሙ ሴቶች መካከል የምትመረጥ ናት፡፡ ይህቺ ሴት የእንግዴ ልጁን ተፈቅፍቆ በደረቀ የእንሰት ግንድ ጠቅልላ ከቤቱ ውስጥ በተዘጋጀ ጉድጉድ ትቀብራለች(ተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ የካቲት 2017 ዓ.ም.)፡፡

መውለድ ያቆመች ሴት እና ደረቅ የእንሰት ግንድ የልምላሜነት ባህርይ ያጡ እንደመሆናቸው ህይወት አልባነትን ወክለው ይመጣሉ፡፡ ህይወት አልባውን የእንግዴ ልጅ በተመሳሰሎ በሚመጡ አካላት ይወገዳል፡፡ የሚወገደው ደግሞ በአባት ቤተሰቦች መኖሪያ ውስጥ ነው፡፡ ይህም ከላይ እንደቀረበው የአባት ደም አካል እንደመሆኑ ከቤት አይወጣም፡፡ ከላይ የቀረበው የወሊድ ቀን ሁነት በአሁኑ ወቅት የሚተገበር አለመሆኑ በምልከታ ወቅት ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የሚተገበረው የወሊድ ቀን ስርዓት የሚጀምረው ወላዷን በመቀበል ነው፡፡ ወላዷ ወደ መታረሻ ቦታዋ ስትገባ ቤት ውስጥ የሚጠብቋት ሴቶች እልልታ ይቀበሏታል፡፡ በዚህ ወቅት በሚቀበሏት ሰዎች ፊት ላይ የሚታየው የደስታ ስሜት መወለድ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ዋጋ እንደሚያሳይ በምልከታ ወቅት ተስተውሏል፡፡ ወደ ማረፊያዋ ከደረሰች በኋላም የመጀመሪያ ምግብ የመቅመስ ስርዓት ወይም ካጫ ታካሂዳለች፡፡ ይህን ምግብ የሚሰሩት ከለጋ ቡላ ሲሆን ቅቤ እንደሚገባበት ወ/ሮ አበበች ገልፀዋል(ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ የካቲት 2017 ዓ.ም)፡፡ ይህንን ምግብ በመንደሩ ውስጥ በእድሜ ትልቅ የሆኑ ሴት ሶስት ጊዜ ያጎርሷታል፡፡ ከሶስተኛው ጉርሻ በኋላ በእጇ መጉረስ እንደምትጀምር ለመመልከት ተችሏል( ዶርዜ ሄርጶ፣ የካቲት 2017 ዓ. ም.)፡፡ ሶስት እንደ ነገር ማፅኛ ሆኖ ይመጣል፡፡ ይህ ድርጊት ወደ እናትነት መምጣቷን እንደማለማመጃ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ የመጀመሪያ ምግብ ሆኖ የሚመጣው ቡላ ለስላሳ መሆኑ እና በቀላሉ ለመመገብ አመቺ መሆኑ እንደምክንያት ይነሳ እንጂ ከዚህ የዘለለ አንድምታ እንዳለው በአዘገጃጀት ሂደቱ ማየት ይቻላል፡፡ የቡላ ዝግጅት ከመጀመሪያ እስከ ፍፃሜው ድረስ በሴቶች የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ነው፡፡ በዶርዜ ማህበረሰብ የምግብ ስርዓቶች ውስጥም በስፋት ይስተዋላል፡፡ ምግብ የማቅመስ ስርዓቱ የሚጀመረውም በዚሁ ቤት ባፈራው የምግብ አይነት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በሚኖረው የመታረስ ሂደት ውስጥ ግን በባል አቅራቢነት በሚዘጋጁ ምግቦች እንደምትታረስ በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ ባሉ የማረስ ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉ ሴቶች ሲሆኑ አባት የሚያስፈልጉ ነገሮች ሲኖሩ በማቅረብ ይሳተፋል፡፡

በዛው ቀን ወላዷን መጥተው ደስታዋን የሚካፈሉ ሴቶች በሙሉ ቅቤ ይቀባሉ፤ እርጥብ ሆነናል እናንተም እርጥብ ሁኑ እንደማለት ነው፡፡ የእርጥብነት ጉዳይ ከሴቶች ጋር የሚያያዝ መሆኑን ከሚያመለክቱ ትዕምርቶች

መካከል ይህ አንዱ ነው። እርጥብነት ዘርን ወደፍሬ ለመቀዬር በሚደረግ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው። በተለያዩ ማህበረሰብ ዘንድ የወሊድ ስርዓቶች በሴቶች በሚከወኑ ሁነቶች የሚበዛበት እንደሆነ ይጠቀሳል። ይህም በተለይ የሴት ተፈጥሮን የሚመለከቱ ጉዳዮች የሚስተዋልበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደሆነ ይታመናል።

በጊዜ ወሊድ ከበራ ውስጥ ስርዓተ-*ፆታን* ከሚያመላክቱ ሁነቶች ውስጥ ሌላው የሚጠቀሰው ከተወለደው/ችው ህፃን *ፆታ* ጋር ተያይዘው በሚጠይቁ ሰዎች የሚነገሩ አባባሎች ናቸው። አራሷን ለመጠየቅ የሚመጡ ሰዎች እንደተወለደው ልጅ *ፆታ* ደስታቸውን የሚገልጡበት አባባል የተለያዬ ነው። የተወለደችው ሴት ከሆነች “ትሁን” የሚባል ሲሆን ወንድ ሲሆን ደግሞ “እሰይ ዘር የሚያበዛ ወለድሽ ዘር ሊሰፋ ነው” ይባላል።

> ወንድ ልጅ ሲወለድ እኛ አካባቢ በጣም ክብር ነው በጣም ቦታ ይኖረዋል.... ወንድ ልጅ ወለደች ከተባለ *ሰዬ ኤሊና ሰንጮ* ይባላል... በቃ ወንድ ወለደች ከተባለ በቃ ወራሽ ተወልዷል የሚለውን ነገር ነው የሚያሳየው *ታካይሬሲ* ይላል ራሱን ወልዷል ይባላል.... ሴት ስትሆን ትደግ ነው የሚሉት ለእሷ ትደግ ለእሱ ትደግ የምታጠጣን አግኝተናል ነው የሚባለው።ወንድ ልጅ ደግሞ ቦታ ይኖረዋል(ወ/ሮ ወላሄ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ አማራ፣ መስከረም 2018 ዓ.ም.)

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው የሴት ልጅ መወለድ እንደወንዱ አይነት የደስታ ስሜትን አይፈጥርም፤ በተለይ ወንድ ባልተወለደበት ቤት። ይህን የሚገልፅ ስሜትም በተለይ በአባት እንዲሁም ሊጠይቁ በሚመጡ ሰዎች ዘንድም በምልከታ ወቅት ማስተዋል ተችሏል። ይህም ተተኪ እና ተረካቢ ካለማግኘት ጋር ይያዛል። ይህንንም አቶ አባይነህ ከሚከተለው የአቶ አባይነህ ሃሳብ እንረዳለን።

> ከሴት በላይ ወንድ ሲወለድ ነው ደስታው ለምን ሴት ብትወለድ አግብታ ባሏ ቤት ነው የምትቀረው። ወንድ ነው ስም የሚያስጠራው ሴት ወደሌላ ሂያጅ ስለሆነች በሴት ብዙም ሰው ደስተኛ አይደለም። ወንድ ከተወለደ ጎበዝ እናት ትባላለች ሴት ትሄዳለች ወንድ ነው እቤት ቀርቶ እርስትነን የሚረከበው እና ስም የሚያስጠራው ለዛ ነው(ዶርዜ ሄርጶ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.)

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሴት የቤተሰቧ የምትሆነው ትዳር እስክትመሰርት በመሆኑ ቋሚ አይደለችም። በተቃራኒው ወንድ ልጅ የቤተሰቡን ርስት ተረካቢ እና ጧሪ ነው። በማህበረሰቡ ዘንድ የወንድ ልጅን አስፈላጊነት አቶ አራቤ “ውርስን ለመከላከል ነው ወንድ ልጅ ይፈጠር የሚባለው ... ስም እንዳይጠፋ ለማድረግ ነው። ያው ካልሆነ ንብረቱን ከጎን የነበረ ወንድም ወይም የአጎት ልጅ ምናምን ይወርሳል...”(ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም)በማለት ያስረዳሉ። ይህም አባት ከአባቱ የወረሰውን ርስት እና ስም ለማስቀጠል ብቸኛ ምርጫው ወንድ ልጅ መሆኑን ያሳያል። ሴት ብቻ ተደጋግሞ በተወለደባቸው ትዳሮች ውስጥ ድርብ ጋብቻን ማሰብ

ወራሽ ለማግኘት የሚደረግ አማራጭ እንደሆነም በቃለመጠይቅ እና ተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እንደ አቶ ተክሉ ገለፃ "ደጋግማ ሴት ከወለደች አንቺ ለኔ የሚወርሰኝን አልወለድሽም ሌላ እንዳገባ ፍቀጅልኝ" በማለት ፍቃድ ካገኘ ድጋሚ ያገባል(ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ አማራ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.)፡፡ ድርብ ጋብቻው ካልተፈለገም የወንድምን ልጅ በጉዲፈቻ በመውሰድ ወራሽ ልጅ እንደተገኘ ይቆጠራል(የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ ሄርጳ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.)፡፡

በዶርዜ ማህበረሰብ ደንብ መሰረት መሬት የሚወርሰው ወንድ ልጅ ብቻ ሲሆን፣ ወንድ ልጅ በሌለበት ቤት ደግሞ በወንድ የዘር ሃረግ ውስጥ ያለ ወንድ ዘመድ ይወርሳል (Hebo & Mahari, 2022)፡፡ በመሆኑም ሴት ብቻ መውለድ ካለወራሽ ከመቅረት ጋር ሲያያዝ፤ ወንድ መውለድ ደግሞ ተተኪ ማግኘትን ያመለክታል፡፡ ወንድ ከመወለዱ ጋር ተያይዞ የሚባሉ አባባሎችም ይህንን የማህበረሰቡን የቆየ ልማድ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይህንም Qiu(2023) አባዊ ስርዓትን በሚከተሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ወንድ ልጅ ከትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣን ውርስ ተቀባይ፣ የዘር ሃረግን አስቀጣይ እና ጎሳውን አስፊ ከመሆን ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ካነሱት ሃሳብ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በወሊድ ከበራው ውስጥ ወንድ ልጅ ሲወለድ የአያት አቀባበል ሌላው በወሊድ ጊዜ ከሚከሰቱ እና ስርዓተ-ፆታን አመላካች የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የሚከሰተው አዲስ የተወለደው ልጅ አያት በቤት ውስጥ ባልነበረበት ወቅት ከተወለደ ነው፡፡ በመሆኑም አያት ከነበረበት ወደቤቱ ሲመጣ የተወለደው ህፃን ወንድ መሆኑን ሲያውቅ *በወንድ ላይ ወንድ ተወለደ* በማለት የህፃኑ አያት በቀጥታ ወደ ቤት አይገባም፡፡ ይልቁንም ከግቢው በር ላይ ቆሞ *"ኦኔ ታሶ ናዲ ኣዴትራ?"* ይላል *"በኔ ቤት ማን ወንድ ነው የገባው?"* ማለት ነው (አቶ ተሾመ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ ሄርጳ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.):: የህፃኑ አባትም እናትየውንና ህፃኑን ይዞ ወደ ውጭ ይወጣል፡፡ ከወጣ በኋላ አባት እቤት ገብቶ እንደተቀመጠ እናትየው ልጁን ይዛ እንደአዲስ ትገባና ታሳቅፈዋለች፡፡ እሱም ልጁን ይዞ ይመርቀዋል፡፡ ወንድ የቤቱ ራስ እንደመሆኑ ይህን ስልጣኑን ሊጋፋው የሚችለው ሌላ ወንድ ሲመጣ እንዲሁ የማይቀበል መሆኑን የሚያሳይ ሁነት መሆኑን በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኘው ማስረጃ ያመለክታል (ዶርዜ ሄርጳ፣ የካቲት 2017 ዓ.ም.)፡፡ በማህበረሰቡ ልማድ መሰረት መሬት እና ቤት የወንድ መሆኑ ይታመናል (Hebo & Mahari, 2022; Olmstead, 1975)፡፡ በመሆኑም ከላይ የቀረበው ሁነት ከወራሽነት እና ተተኪነት ጋር የሚያያዝ መሆኑን መገንዘብ ያስችላል፡፡

በዶርዜ ማህበረሰብ የወሊድ ከበራ ውስጥ ስርዓተ-ፆታን አመላካች ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ሌላው አቅጣጫ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ወንድ ወይም ሴት መወለዱን በአቀማመጥ አቅጣጫ ማወቅ ይቻላል፤ ወንድ ከሆነ በቀኝ በኩል ሴት ከሆነች ደግሞ በግራ በኩል ይተኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም

ጠያቂ ሲገባ አባት ተነስቶ ወንድ ከሆነ በቀኝ፤ ሴት ከሆነች ደግሞ በግራ እንዲቀመጡ ይጋብዛል፡፡ እንደማህበረሰቡ እይታ መሰረት የዚህን ሁነት ምክንያት ከተፈጥሮ ጋር ያገናኙታል፡፡

> እኛ አይደለንም ይህን ያመጣነው ተፈጥሮ ነው እኛ ራሱ ስናረግዝ ወንድ በቀኝ በኩል ሴት ደግሞ በግራ በኩል ነው የሚሆኑት እና በባህላችን ወንድና ሴት መሆናቸውን አርግዘን ነው የምናውቀው ይሄ ተፈጥሮ ነው ለዛ ነው ወንድ ተወልዶ ሲመጣ በቀኝ ተቀብለን በቀኝ በኩል ሴት ከሆነች በግራ ተቀብለን በግራ በኩል የምናስተኛው ይሄ የእግዚአብሄር ስራ ነው(ወ/ሮ አበበች፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ ሄርጾ፣ ህዳር ፣ 2017 ዓ.ም)

ተፈጥሮ የፈጣሪ ስራ የሚገለጥበት እንደመሆኑ ከፈጣሪ ስርዓት ላለመውጣት የሚደረግ ጥረት አካል ተደርጎ እንደሚቆጠር ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንረዳለን፡፡ የቀኝ እና ግራ ጉዳይ በወሊድ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሁነቶች ውስጥም ይስተዋላል፡፡ ለአብነት ያህልም በድቡሻ ውስጥ በሚካሄዱ ሁነቶች እና በለቅሶ ክዋኔዎች ላይ ተመሳሳይ እይታዎች ተስተውለዋል፡፡ በወሊድ ወቅት ወንዶች በቀኝ መሆናቸው ምንም እንኳን ተፈጥሯዊ መላምትን መሰረት ያደረገ ቢሆንም፤ በሌላ ሁነት ውስጥ ግን ተመራጭነትን እና ወራሽነትን ወክሎ ይመጣል፡- በማህበረሰቡ የጋብቻ ባህል ወራሽ ለሚሆን ታላቅ ወንድ የጫጉላ ቤት የሚሰራው በቀኝ በኩል ሲሆን ተከታዮች ደግሞ በግራ በኩል ይሰራላቸዋል፡፡ የአባትን ርስት የሚወርሰው እና የአባት ተተኪ ተብሎ የሚታመነው ታላቅ ወንድም ነው፡፡

ቀኝ በሰው ልጆች ዘንድ ለስራ ተመራጩ እንደመሆኑ የጥንካሬ እና የክህሎት ባህሪያትን የተላበሰ መሆኑን የሚያነሱት Hertz (2013)፤ ቀኝ የአካል ጥንካሬን፣ አዕምሯዊ ብስለትን፣ ወሳኝነትን፣ መልካም እድልን እና ህጋዊነትን ለመግለፅ የሚያገለግል ሲሆን ግራ በተቃራኒ የሚመጡ ሃሳቦችን የሚወክል መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በተለያዩ የሐይማኖት አስተምህሮዎችም የቀኝ እና ግራ ውክልና ከዚህ ብዙም የተለዩ እንዳልሆኑ ይታያል፡፡ Rosas እና Ferreira(2013) በክርስትና ውስጥ ካለው አስተምህሮ በመነሳት ቀኝ ፅድቅን እና ተመራጭነትን፣ ግራ ሃጥያትን እና አለመመረጥን የሚወክሉ ትዕምርታዊ አቅጣጫዎች መሆናቸውን ያብራራሉ ፡፡ ከዚህ በተመሳሳይም Couzin(2021) ቀኝ ጥንካሬን፣ እውነትን እና የበላይነትን፤ ግራ ደግሞ አቅም ማጣትን፣ የበታችነትን እና ድጋፍ ፈላጊነትን የሚወክል ትዕምርት መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ በመነሳትም በዶርዜ ማህበረሰብ የወሊድ ስርዓት ውስጥ የሚገኘው ወንድን በቀኝ ሴትን ደግሞ በግራ የማድረግ ልማድ የወንድን ተመራጭነት፣ ባለ ርስትነት፣ ተፈላጊነት እና የበላይነት የሚያመላክትቱ ሲሆኑ፤ የሴትን ደግሞ በተቃራኒው የሚያሳይ ነው፡፡

**ድህረ - ወሊድ**

ይህ ክፍል በዋናነት ከወሊድ በኋላ የሚመጣውን የጋዮ ጋዶ(ገበያ[1] የማስገባት) ስርዓትን ይመለከታል፡፡ በዶርዜ ማህበረሰብ ዘንድ አንዲት የወለደች ሴት የአራስነት ጊዜዋን የምትጨርሰው ከ40 ወይም ከ80 ቀናት በኋላ ክርስትና ስታስነሳ ነው[2]፡፡ አራስነቷን ጨርሳ ወደማህበራዊ ጉዳዮች ለመሳተፍ ግን ወልዳ ስትመለስም ገበያ ገብታ ማህበረሰባዊ እውቅና ማግኘት አለባት፡፡ ይህ ስርዓትም ጋዮ ጋዳ ይባላል፡፡የወላዷ ዘመዶች እና ጎረቤቶች እናትን አጅበው ወደ ገበያው ቦታ ይወስዷታል፡፡ ቦዶ ገበያ ሴቶች ገበያ ሲገቡ የተለያዩ ማህበራዊ መረጃዎችን የሚለዋወጡበት እና እንደ ሶፌ እንዲሁም ጋዮ ጋዳ ስርዓቶችን የሚከውኑበት ራሱን የቻለ ስፍራ አለ፡፡ ይህ ስፍራም በስርዓት በተደረደሩ የድንጋይ መቀመጫዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ ወላዷ እና ከአጃቢዎቿ ገበያ እንደደረሱም ለተለያዩ በዚህ ስፍራ ኮባ ተነጥፎ እንድትቀመጥ ይደረጋል፡፡ አጅበዋት የሄዱ ሴቶችም ዙሪያዋን ይቀመጡና ለዝግጅቱ ተብሎ የተወሰደው መጠጥን እየጠጡ ይጫወታሉ፡፡ ታላላቆች ከመረቋት በኋላም የዝግጅቱ ፍፃሜ እንደሆኑ በምልከታ ታይቷል(ቦዶ ገበያ፣ የካቲት እና ሚያዚያ 2017 ዓ.ም.) ፡፡

ይህም ወላዷ ተለይታው ከነበረው ማህበረሰባዊ ግንኙነት የመቀላቀያ ሁነት እንደመሆኑ፤ ከዚህ ቀን በኋላ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የመሳተፍ መብቷን ይመለስላታል(የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ ሄርጾ፣ የካቲት 2017 ዓ.ም.)፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ የሚቀርበውን መጠጥ የወንድ ወገን የሚያመጣ ይሆናል፡፡ እንደ Ellen(2012) ገለፃ በአብዛኛው የወሊድ ስርዓት ውስጥ የወንድ ወገን ለሴት ወገን ግብዣ እንደሚያደርጉ፤ ይህም የወንድ ወገንን እንደአቅራቢ የሴት ወገንን ደግሞ እንደተቀባይ እንደሚያሳይ ይጠቅሳሉ፡፡ በዶርዜ ማህበረሰብም ከጋዮ ጋዳ ቀን በተጨማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ አራሷን ሊጠይቁ ለሚመጡ የሴት ወገኖች ግብዣ ይደረግላቸዋል፡፡ ነገር ግን የሴት ወገን ከወንድ ወገን የቀረበውን ግብዣ ተቀብሎ ብቻ የሚቀር ሳይሆን በዚያው ልክም መልሶ አቅራቢ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳን ጀማሪው የወንድ ወገን ቢሆንም የሴት ወገንም በቀጣይ ባሉ የገበያ ቀናት እንዲሁም ከመጀመሪያው ጥየቃ በኋላ ባሉ ተከታታይ ሳምንታት የመጠጥ ግብዣ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ በመነሳትም የሰጥቶ መቀበል እና የተቀብሎ መስጠት ጉዳይ በወንድ እና ሴት ሚናዎች ውስጥ ታይቷል፡፡

ሴት ልጅ ለቤተሰቦቿ የሚኖራት ድርሻ እስክታገባ ድረስ ነው፡፡ ከዛ በኋላ ያለው ጊዜዋን የምታሳልፈው በባሏ ቤተሰቦች አካባቢ ነው፡፡ ይህም አብዛኛውን

---

[1] በዶርዜ ማህበረሰብ ዘንድ ገበያ የመገበያያ ቦታ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የሚፈፀሙበት ባህላዊ ስፍራም ጭምር ነው፡፡ ዶርዜ ገበያ ቀናት ሰኞ እና ሀሙስ ሲሆን በገበያ የሚደረጉ ስርዓቶች የሚፈፀሙት በእነዚህ ቀናት ነው፡፡ በእነዚህ ቀናት ከተለያ ጎሳዎች የሚመጡ ሰዎች ከሚያከናውኑት ግዢ እና ሽያጭ በተጨማሪ በመስቀል ሰሞን የሶፌ ስርዓትን በሌሎች ጊዜያት ደግሞ የጋዮ ጋዳ ስርዓትን የሚፈጽሙ ሰዎችም በስፍራው ይገኛሉ፡፡

[2] የ ዶርዜ ማህበረሰብ በአብዛኛው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ነው፡፡

የህይወቷን ክፍል መጀመሪያ ባሏን እና የባሏን ቤተሰቦች ቀጥሎም የራሷን ልጆች በመንከባከብ እንድታሳልፍ ያደርጋታል፡፡ በማህበረሰቡ የጋብቻ ስርዓት መሰረት አንዲት ሴት ካገባች በኋላ እንድትኖር የሚፈቀድላት በባሏ ቤተሰቦች አካባቢ ነው፡፡ የምትኖረውም ወንዶች በባለቤትነት በሚያስተዳድሯቸው ቦታዎች ነው፤ በአባቷ አልያም በባሏ፡፡ ለዚህም ይመስላል "*አይደካ ማጫይ አይርክ*" ወይም "ዞሮ ዞሮ ሴት የወንድ ናት" የሚል አባባል የሚነገረው፡፡ ከሁለቱም ወገን የቋሚ ንብረት ውርስ አታገኝም፡፡ በአብዛኛውን ማህበረሰብ የዘር ሃረግ የሚመዘዘው በወንድ ወገን መሆን፣ ያገቡ ጥንዶች ከወንድ ወገን ቤተሰብ ጋር አልያም አካባቢ እንዲኖሩ የሚፈቅድ ስርዓት መኖር፣ የቋሚ ንብረት ውርስ ደንቡ ለወንዶች ብቻ መሆኑ ሴቶች በሚገቡበት ቤተሰብ ውስጥ እንዲኖሩ ያደርጋል የሚል ሃሳብን Lindsey (2016) ያነሳሉ፡፡ በዶርዜ ማህበረሰብ የወሊድ ከበራዎች ውስጥ የታዩት በባል ቤተሰብ ቤት የመውለድ እና መታረስ፣ እንደተወለደው/ችው ህፃን ፆታ ልዩነት የሚባሉ አባባሎች፣ የአያት አቀባበል እና በአጠቃላይ ሁነቶች ውስጥም የወንድ የወራሽነት እና ተተኪነት፣ የባለቤትነት እንዲሁም የአቅራቢነት ሚናዎች በስፋት ተስተውለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሴቶች ሚና በዋናነት ከተንከባካቢነት ጋር ተያይዞ ታይቷል፡፡

## ማጠቃለያ እና መደምደሚያ

ይህ ጥናት የዶርዜ ማህበረሰብን የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች አቀራረፅ በወሊድ ከበራው አማካኝነት እንዴት እንደተቀረፁ የመረመረ ነው፡፡ የወሊድ ከበራው አንድም እናትዬውን እንዲሁም ህፃኑ/ኗን ያማከሉ ናቸው፡፡ በዚሁም መሰረት በወሊድ እና መታረሻ ቦታ ምርጫ፣ የተሳታፊዎች ድርሻ፣ የልጅ አያያዝ እና የእንግዳ አቀማመጥ አቅጣጫ፣ የወንድ አያት አቀባበል እና አራሷን ለመጠየቅ የሚመጡ ሰዎች እንደተወለደው/ችው ህፃን ፆታ አይነት የሚሉት አባባል የማህበረሰቡን የስርዓተ-ፆታ ሚናን አመላካች ሆኖ ቀርቧል፡፡ በእነዚህ ሁነቶች ውስጥም ወንድነትን ከወራሽነት፣ ከተተኪነት፣ ከባለቤትነት እና አቅራቢነት አንፃር ሲታይ ሴትነትን ደግሞ በዋናነት ከተንከባካቢነት አንፃር ታይቷል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች በዋናነት ማህበረሰቡ ከሚከተለው ከጋብቻ አመሰራረት ስርዓት ጋር በተያያዘ ከሚነሱት በባል ቤተሰብ አካባቢ የመኖር፣ በአባት የዘር ሃረግ የመጠራት እና የመሬት እና ቋሚ ንብረቶች የመውረስ መብት የወንዶች ከመሆኑ ጋር የተያያዘ መሆኑ ተስተውሏል፡፡ ይህም የማህበረሰቡን አባዊነት ያሳያል፡፡ ከዚህም በመነሳት ወንዱ በመሬቱ እና በቤቱ ለሚካሄዱ ማንኛውም ጉዳይ ባለመብት ነው፡፡ይህም ወንዶች የውሳኔ ሰጪነት እና አቅራቢነት ሚና እንዲኖራቸው የሚያደርግ መሆኑ በጥናቱ ተገልጧል፡፡ በአጠቃላይ ከመረጃ ትንተናው በመነሳት እንደሚከተለው መደምደም ይቻላል፡፡ የዶርዜ ማህበረሰብ የወንድነት እና ሴትነት ስሪት ሰጥቶ በመቀበል እና ተቀብሎ በመስጠት እሳቤ የተቃኘ ሆኖ

ታይቷል፤ ወንድነትን ሰጥቶ በመቀበል፤ ሴትነት ደግሞ ተቀብሎ በመስጠት። ሰጥቶ በመቀበል ውስጥ በዋናነት የአቅራቢነትን፣ የባለቤትነትን፣ የቀጣይነት እና የውሳኔ ሰጭነትን፤ ተቀብሎ በመስጠት ውስጥ ደግሞ የተንከባካቢነት፣ የደጋፊነት እና የጊዜያዊነት ሃሳቦች ታይተዋል።

**ምስጋና**

ጥናቱ እውን ይሆን ዘንድ በመስክ ረዳትነት፣ አስተርጓሚነት እና መረጃ ሰጪነት ለተባበሩ አካላት በሙሉ ክብረት ይስጥልኝ።

**የጥቅም ግጭት**

ይህ ጥናት ከማንኛውም አካል ጋር የጥቅም ግጭት የለበትም።

## ዋቢ ፅሁፎች


አፀደ ተፈራ፤ (2007)፤ የዋግ ኽምራ የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ስነ-ስርዓት ፋይዳ ትንተና፤ያልታተመ፤ የፒኤችዲ ማሟያ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። http://etd.aau.edu.et/handle/123456789/26475

እታገኝ አስረስ፤ (2017)፤ የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፤ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ፤ ያልታተመ፤ የፒኤችዲ ማሟያ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። https://etd.aau.edu.et/handle/123456789/5696

ድርብወርቅ ብፁ፤ (2007)፤ የጉሙዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓት በማንዱራ ወረዳ፤ ያልታተመ፤ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። http://etd.aau.edu.et/handle/123456789/16356

ፈቃደ አዘዘ፤ ቁዘማ፡- ፎክሎር(ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ፤ (2004)፤ በሺፈራው በቀለ(አርታኢ)፤ *ባህል እና ልማት በኢትዮጵያ*(ገፅ 97-138)፤ አዲስ አበባ፤ ፎረም ፎር ሶሻል ሳይንስ ስተዲስ።

Adane W. S. & Melese S. A.(2023). Birth ritual ceremony in Hadiya culture. *International Journal of Biosciences*, 23(2), 255-263. http://dx.doi.org/10.12692/ijb/23.2.255-263

Aynalem, B. Y., Melesse, M. F., & Bitewa, Y. B. (2023). Cultural beliefs and traditional practices during pregnancy, child birth, and the postpartum period in East Gojjam Zone, Northwest Ethiopia: a qualitative study. *Women's Health Reports*, *4*(1), 415-422. https://doi.org/10.1089/whr.2023.0024

Bell, C. M. (1997). *Ritual: Perspectives and dimensions*. Oxford University Press.

Bem, S. L. (1993). *The Lenses of Gender: Transforming the Debate on Sexual Inequality*. Yale University Press. https://repository.law.umich.edu/cgi/viewcontent.cgi?article=3279&context=mlr

Blakemore, J. O., Brenbaum, S. A. & Liben, L. S..(2009). *Gender Development*. Taylor & Francis Group, LLC. https://doi.org/10.4324/9780203889756

Carter, M. J., & Fuller, C. (2015). Symbolic interactionism. *Sociopedia. isa*, *1*(1), 1-17. https://doi.org/10.1177/205684601561

Couzin, R. (2021). *Right and left in early Christian and medieval art*. Brill.

Das, D. (2022). Gendered Ritual: A Sociological Inquiry into The Construction of Womanhood in The Kamrup-Assam as A cultural Region. *International Journal of Humanities and Social Science Invention.*, *11*(3), 31-39. https://doi.org/10.35629/7722-1103023139

Davis-Floyd, R., & Laughlin, C. D. (2022). Ritual: What it is, how it works, and why.

Dundes, A. (2007). Folk ideas as units of worldview. In, S. J. Bronner (ed.). *The meaning of Folklore: The Analytical Essays of Alan Dundes* (pp. 179-192). Utah State University Press. https://files01.core.ac.uk/download/32550172.pdf

Ellen, R. (2012). *Nuaulu Religious Practices; The frequency and reproduction of rituals in a Moluccan society* (p. 356). Brill.https://www.jstor.org/stable/10.1163/j.ctvbqs3p5

Freeman, D. (2002). *Initiating change in highland Ethiopia: Causes and consequences of cultural transformation*. Cambridge University Press Mathiszig, L. (2014). The dorze weavers of Ethiopia. *Textile*, *12*(2), 180-187. https://doi.org/10.3366/afr.2004.74.4.701

Frobish, T. S. (2004). Ritual as Communication. In F. A. Salamone(ed.). *Encyclopedia of religious rites, rituals, and festivals*(pp.361-362). ROUTLEDGE, Berkshire Publishing Group.

Getaneh M. (2004). The role of women in the household economy: The Dorze case. Addis Ababa, Addis Ababa University. Unpublished. MA Thesis. http://etd.aau.edu.et/handle/123456789/32371

Getaneh M. (2014). Betwixt and Between? Culture and women‟s rights in the context of multiple legal and institutional settings, the Dorze case, southwestern Ethiopia. Addis Ababa University. Unpublished. PhD Dissertation.

Giuliano, P. (2020). Gender and culture. *Oxford Review of Economic Policy*, *36*(4), 944-961. https://doi.org/10.1093/oxrep/graa044

Halperin, R., & Olmstead, J. (1976). To catch a feastgiver: redistribution among the Dorze of Ethiopia. *Africa*, *46*(2), 146-164. https://www.jstor.org/stable/1158758

Hebo, M., & Mahari, G. (2022). Land Tenure Reforms and Women’s Land Rights in Plural ‘Legal’and Cultural Settings: A Comparative Study of the Arsii Oromo and Dorze-Gamo, Ethiopia. *Ethiopian Journal of Development Research*, *44*(1), 39-76. https://www.ajol.info/index.php/ejdr/article/view/242913

Helgeson, V. S. (2012). *The psychology of gender* (4th ed.). United States of America, Pearson Education, Inc. https://doi.org/10.4324/9781315663081

Hertz, R. (2013). The pre-eminence of the right hand: A study in religious polarity. *HAU: Journal of Ethnographic Theory*, *3*(2), 335-357. https://www.journals.uchicago.edu/doi/pdfplus/10.14318/hau3.2.024

Juschka, D. (1999). The category of gender in the study of religion. *Methods &Theory in the Srudy of Religion. 11*(1), 77-105. https://www.jstor.org/stable/pdf/23549690.

Kitila, S., Molla, W., Wedaynewu, T., Yadessa, T., & Gellan, M. (2018). Folk practice during childbirth and reasons for the practice in Ethiopia: A systematic review. *Gynecology Obstetrics*, *8*(465), 2161-0932. https://doi.org/10.4172/2161-0932.1000465

Klingorova, K., & Havlicek, T. (2015). Religion and gender inequality: The status of women in the societies of world religions. *Moravian Geographical Reports*, *23*(2), 2-11. https://doi.org/10.1515/mgr-2015-0006

Kousaleos, N. (1999). Feminist Theory and Folklore. *Folklore Forum*, 30(1/2),19-34. https://www.jstor.org/stable/1500085

Lawton, M. & Primiano, L. N.(1996). Gender and Folklore. In J. H. Brunvand(ed.). *American Folklore: An Encyclopedia*(pp.675-680). Garland Publishing, Inc. https://api.pageplace.de/preview/DT0400.9781135578787_A2

Lewis, D. (2005). African gender research and postcoloniality: Legacies and challenges. In *African Gender Studies A Reader* (pp. 381-395). Palgrave Macmillan US.

Lindsey, L. L. (2016). *Gender Roles A Sociological Perspective* (6th ed.). Taylor & Francis. https://doi.org/10.4324/9781315664095

Lorber, J. (1994). *Paradoxes of Gender*. Yale University Press.

Maponya, D. T. (2021). The African woman's plight of reproduction: A philosophical analysis of marriage, procreation and womanhood. *Agenda*, *35*(3), 82-91. https://doi.org/10.1080/10130950.2021.1972598

Mathiszig, L. (2014). The dorze weavers of Ethiopia. *Textile*, *12*(2), 180-187. https://doi.org/10.2752/175303714x14023922798101

Naik, P. & Sethi, S.(2025). Ritual, Gender and Identity: An Anthropological Perspective. *Indian Journal of Research in Anthropology*. *11*(1): 19-29. https://doi.org/10.21088/ijra.2454.9118.11125.2

Olmstead, J. (1972). The Dorze House: A Bamboo Basket. *Journal of Ethiopian Studies*, *10*(2),27-36. https://www.jstor.org/stable/41965856

Olmstead, J. (1975). Farmer's wife, weaver's wife: women and work in two southern Ethiopian communities. *African Studies Review*, *18*(3), 85-98. https://doi.org/10.2307/523723

Pilcher, J. & Whelehan, I. (2004). *Fifty Key Concepts in Gender Studies*. SAGE Publicstions Ltd. https://sk.sagepub.com/dict/mono/preview/50-key-concepts-in-gender-studies.pdf

Polit, K. (2016). The making of persons and ancestors: Rituals of birth and death among Dalits in the Garhwal Himalayas. *Childbirth and Its Accompanying Rituals. Heildeberg: Draupadi Verlag*, 59-86. https://doi.org/10.15496/PUBLIKATION-57157

Pollock, K. T.(2004). Gender Rituals. In F. A. Salamone(ed.). *Encyclopedia of Religious rites, rituals, and festivals*(pp.145-149). ROUTLEDGE, Berkshire Publishing Group.

Qiu, R. (2023). Traditional gender roles and patriarchal values: Critical personal narratives of a woman from the Chaoshan region in China. *New Directions for Adult and Continuing Education*, *2023*(180), 51-63. DOI: 10.1002/ace.20511

Reddock, R. (2000). Why gender? Why development. In J. L. Parpart, P. Connelly & E. Barriteau (Eds.). *Theoretical perspectives on gender and development*(pp. 23-50). IDRC. http://hdl.handle.net/10625/29659

Risman, B. J. (2018). Gender as a social structure. In *Handbook of the Sociology of Gender* (pp. 19-43). Springer International Publishing. https://doi.org/10.1177/0891243204265349

Risman, B. J & Davis, G.(2013) From Sex Role to Gender Structure. *Current Sociology Review, 61*(5-6): 733-755. https://doi.org/10.1177/0011392113479315

Rosas, J. C., &. Ferreira, A. R (Eds.). (2013). *Left and Right: The Great Dichotomy Revisited*. Cambridge Scholars Publishing.

Saikeneva, D.(2024). Giving birth rituals of Qazaq and Chinese: some aspects of gender difference.*Qazaq Historical Review*, 2(3): 308–321 (in Russian). DOI: https://doi.org/10.69567/3007-0236.2024.3.308.321

Salamone, F. A.(2004). Symbol and Ritual. In F. A. Salamone (ed.). *Encyclopedia of Religious rites, rituals, and festivals*(pp.424-425). Berkshire Publishing Group.

Sawin, P. E.(1997). Gender. In T. A. Green(ed.) *Foklore an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art(pp*.405-408). California.

Sims, M., & Stephens, M. (2011). *Living folklore: An introduction to the study of people and their traditions*. Utah State University Press. https://bpb-us-e1.wpmucdn.com/wordpressua.uark.edu/dist/b/596/files/2016/05/Living-Folklore-2nd-Ed.-Sims-Stephens.pdf

Solomon, N., & Tesfaye, M. (2022). Traditional practices during pregnancy and childbirth among mothers in Shey Bench District, South West Ethiopia. *SAGE Open Medicine*, *10*, 20503121221098139. https://doi.org/10.1177/20503121221098139

Van Beek, W. (2002). Why a twin is not a child: Symbols in Kapsiki birth rituals. *Journal des africanistes*, *72*(1), 119-147. https://doi.org/10.3406/jafr.2002.1290

Wagaye W.(2016). Indigenous Knowledge of Herbal Medicine and Healing Practice Among the Gamo People: The Case of Dorze Dere Southern Ethiopia. Addis Ababa, Addis Ababa University. Unpublished MA Thesis. http://etd.aau.edu.et/handle/123456789/3292

Wienclaw, R. A.(2011). Gender Roles. In *GENDER ROLES & EQUALITY*(pp. 33-40). Salem Press.

West, C. & Zimmerman, D. H. (1987). Doing Gender. *Gender and Society*, *1*(2): 125-151. https://www.jstor.org/stable/189945

Wood, W. & Eagly, A.H.(2012). Biosocial Construction of Sex Differences and Similarities Behavior. In J. M. Zanna's, *Advances in Experimental Social* (pp. 55-123). iAcademic Press: Elsevier Inc. https://doi.org/10.1016/B978-0-12-394281-4.00002-7

Woodhead, L. (2012). Gender differences in religious practice and significance. *Travail, genre et sociétés*, *27*(1), 33-54. https://doi.org/10.3917/tgs.027.0033